# ባራክ ኦባማ የሚቀጥለው የአሜሪካ ፕሬዚደንት ?

ለአንድ ሳምንት ያህል አፍጋኒስታን ደርሶ ፣ ኢራቅን ከዚያም እስራኤልንና ፓለስቲናን አዳርሶ ፣ አማን የጆርዳን ዋና ከተማ ገብቶ ከጥቂት ጊዜ ጉብኝት በኋላ ለጋዜጠኞች ለቀረበለት ጥያቄ መልስ የሰጠው ባራክ ኦባማ በ24.07.08 በርሊን የጀርመን ዋና ከተማ በመድረስ ከቻንስለሯ ከወይዘሮ መርክልና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስተሩ ከአቶ ሰታይን ማየር ጋር ሰለ ወደ ፊቱ የአውሮፓና የአሜሪካ ግኑኝነት ሁኔታ ተነጋግሯል።

ባርክ ኦባማ ወደ አውሮፓ ከማምራቱ ቀደም ብሎ በርሊን ብራንደን ጌት ፊት ለፊት የወደፊቱ የአውሮፓና የአሜሪካ ግኑኝነት ሊታደስ የሚችልበትን ሁኔታ ንግግር ለማድረግ እንደሚፈልግ በምርጫው አዘጋጂዎቹ አማካይነት የበርሊንን አስተዳደር መጠየቁ ይታወሳል። ከበርሊኑ ከንቲባም ሆነ ከጀርመኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ፣ እንዲሁም ከብዙ ፖለቲከኞችና ፓርቲዎች ይህ ንግግር ታሪካዊ መሆኑና ብራንደን ጌት ፊት ለፊት ንግግሩ ቢደረግ ፈቃደኛ መሆናቸውን ሲያመልክቱ ፣ ወይዘሮ መርክል ግን እንደማይስማሙ ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል። በሳቸው ዕምነት ፣ ብራንደን ጌት ፊት ለፊት ንግግር ማድረግ የሚችለው ገና ያልተመረጠ ሰው ሳይሆን በስልጣን ያለ መሆን አለበት የሚል ነው። ባራክ አቦማን ከሚደግፉ ፖለቲከኞችም ሆነ ጋዜጠኞች የተሰጠው አስተያየት ፣ ወይዘሮይቱ የባራክን ንግግር በብራንደን ጌት ፊት ለፊት ማድረግ የታቃወሙት ከፕሬዚደንት ቡሽ ጋር ያላቸውን የቀረበ ግኑኝነትና የፓርቲ ፖለቲካ ስምምነት ላለማሻከር ነው የሚል ነው። ሁለተኛው ግምት ፣ ለጊዜው በጀርመን ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እያጣ የመጣው የሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ሁኔታውን ተጠቅሞ ፣ „አዎ እንችላለን“ የሚለውን መፈክር የሱ በማድረግ ለፖለቲካው ይጠቀምበታል ብለው ስለፈሩ ነው የሚል ነው። ያም ሆነ ይህ ባራክና የምርጫ አዘጋጅ ኮሚቴው የወይዘሮ መርክልን ቅሬታ ግምት ውስጥ በማስገባት ንግግሩን የድል ሀውልት እየተባለ በሚታወቀው ስር እንደሚያደርግ ያስታውቃል።

ባራክ ኦባማ ወደ አውሮፓ እንደሚመጣና በተለይም ደግሞ በርሊን ንግግር እንደሚያደርግ ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ ስለ ጉብኝቱና ንግግር ለማድረግ ስለመፈለጉ ጉዳይ በጋዜጣም ሆነ በቴልቪዢንና በሬዲዮ ይወራ ነበር። ጉብኝቱንም ሆነ ንግግሩን በብዙ መቶ ሺህ የሚገመት ህዝብ በጉጉት እንደሚጠባበቅ ተገምቷል። ባራክ ኦባማ በጀርመንም ሆነ በሌሎች የአውሮፓ አገሮች ተቀባይነት ያለው ለመሆኑና ባለፉት ሰባት ወራት ባደረገው ዲሲፒሊንና ጥንካሬ የተሞላበት የፕሪማሪ ውድድር በህዝብ መንፈስ ዘንድ አንድ የተስፋ ጭላንጭል እንዳሰደረ ማወቅ ይቻላል። በየፕሪማሪው ምርጫ ላይ ያደረጋቸውና በተለይም ከነፍስ አባቱ ከሬበርንድ ራይት ጋር በነበረው ግኑኝነት ወረፋ ከደረሰበት በኋላ ባደረገው ሰፋ ያለና ታሪካዊ ንግግር በብዙ ወጣት የጀርመን ህዝብ ዘንደ ተቀባይነት አስገኝቶለታል። ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝብ የሱን መመረጥ ሲፈልግ ፣ አንዳንድ ጋዜጠኞት ደግሞ „አንድ ባራክ ኦባማ ለጀርመን ያስፈልጋል“ እያሉ የሱን መንፈስ የሚስብና ተስፋ የሚሰጥ ንግግር እየተነተኑ በጀርመን ፖለቲከኞች ላይ ያላቸውን ዕምነት ማጣት በግልጽ ይጽፉ ነበር። በሌሎች የአውሮፓ አገሮችም ተቀባይነት ያለውና እነ ፕሬዚደንት ሳርኮሲ ሁሉ ሳይቀሩ ልክ የተመረጠ ፕሬዚደንት ይመስል አብረው ጋዜጣዊ መግለጫ በመስጠት ባራክ በህዛባቸው ዘንድ ተቀባይነት ያለውና እነሱም ፖለቲካዊ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በተዘዋዋሪ ሁኔታውን ለመጠቀም ሽር ጉድ ሲሉ ታይተዋል።

ባራክ አቦማ ከማዕከለኛው ምስራቅ ጉዞው ወደ በርሊን ከመጣና የግማሽ ቀኑን ዝግጅቱን ካጠናቀቀ በኋላ በአውሮፓ የሰዓት አቆጣጠር በ19 ሰዓት በድል ሀውልት ስር ንግግሩን ያደርጋል። ንግግሩን ለማዳመጥ ከሁለት መቶ ሺህ ህዝብ በላይ ሲካፈል ፣ ከሌሎች የጀርመን ከተሞችና የአውሮፓ አገሮችም ብዙ ሰዎች እንደመጡ ማወቅ ተችሏል። በዕለቱ ማህል ከተማው ጥቅ ከማለቱ የተነሳ ለዝግጅቱ ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል። ይህ ሁሉ ሰው ከየቦታው መጉረፍና ንግግሩን ለማዳመጥ በጉጉት መጠባበቅ የአውሮፓው ህዝብ የቱን ያህል እጅ ለእጅ ከሚልና ተንኮል ከተሞላበት ፖለቲካ ለመላቀቅ እንደሚፈልግ ማንበብ ይቻላል። ስለዚህም ባራክ አባማን እግዚአብሄር ከሰማይ ዱብ አድርጎ የጣለው ፣ በህይወት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ሊገኝ የሚችልና ጥሩ መንፈስ ያለው ፖለቲከኛ አድርጎ የሚገምተው ህዝብም ሆነ በፖለቲከኞች ተስፋ የቆረጠው ወጣት በጣም ጥሩ ንግግር እንደሚሰማ ይጠባበቅ ነበር። የድንፋታ ሳይሆን የተስፋና የሰላም ንግግር እንዲሁም ደግሞ

አንድ ቀን ጥሩ እንቅልፍ ተኝቶ ፣ ጥሩ ህልም አልሞ ፣ እንደዚህም ዐይነት ነገር አለ ብሎ ከተሰፋ መቁረጡ ተላቆ የወደፊት ብርሃንን የሚጠባበቀው ህዝብ ብዙ እንደነበር መገመት ይቻላል። ንግግሩን ከሚያደርግበት ቦታ ሲደርስ ሌፕ ቶፑንና ዲጂታል እንዲሁም ቪዲዮ ካሜራውን ይዞ ፎቶ ለማንሳት አንገቱን ወደ ላይ ከፍ አድረጎ የሚጠባበቀውን ለተመለከተ ዕውነትም ህዝቡ የድሮው የጦር ፖለቲካ እንደሰለችውና ከዚህ ሰው አንድ ተአምር ይጠባበቅ ይመስል ነበር። ባራክ ኦባማ ንግግሩን ያደርጋል በተባለው ሰዓት ሳይሆን አስራ አምስት ደቂቃ ዘግይቶ ቀስ ቀስ እያለ ወደ ንግግር ማድረጊያው መድረክ ሲጠጋና እጁን ወደ ላይ እያደረገ ሰላምታ ሲሰጥ የሚሰማው የደስታ ጩኸት በቃላት ለመግለጽ ያስቸግራል። የህዝቡን የደስታ ድምጽ ለማቆም ቢያንስ ከአምስት ጊዜ በላይ አመሰግናለሁ እያለ ወደ ንግግሩ ለመምጣት ይጥር ነበር። ንግግሩን ይጀምራል። ንግግሩም ያተኮረው በጀርመንና በአሜሪካን መሀከል ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ስለተመሰረተው የጠበቀ ግኑኝነት ሲሆን ፣ ጦርነቱ ከማለቁ በፊት ሁለቱም ጠላቶች ሆነው ይዋጉ እንደነበርና ይህ ሁሉ ነገር ተረስቶ አሜሪካን የጀርመን ህዝብ በጊዜው በደረሰበት ጥቃት ስለተጎዳና ይህንን በመረዳቷ በተከታታይ የአውሮፕላን ዕርዳታ ምግብና መድሃኒት በማመላለስ ለጀርመን ህዝብ ፣ በተለይም ደግሞ ለበርሊን ከተማ ህዝብ እንደደረሰችለት የሚያትት ነበር። በመሆኑም ጀርመን በዚህ ዐይነቱ ዕርዳታና በኋላ ደግሞ በማርሻል ፕላን እየተረዳች በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢኮኖሚዋን መገንባት እንደቻለችና ህዝቡም ነጻነትን መቀዳጀት እንደቻለ ያትታል። ይህ ዐይነቱ ግንባታና ነጻነት በኋላ ደግሞ የሰሜን አትላንቲክ የጦር ስምምነት ተመስርቶ አውሮፓና አሜሪካ እንዴት አድርገው በሶቭየት ህብረት የሚመራውን የኮሙኒስት ርዕየተ-ዓለም በጋራ እንደተቋቋሙና አሜሪካንም በግንባር ቀደምትነት ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተች ያመለክታል። በዚህ መልክ በመግቢያው ላይ ባደረገው ሰፊ ሀተታና በኋላ ላይም ወደ ፊት ጀርመንና አሜሪካ ብቻ ሳይሆኑ ፣ አውሮፓና አሜሪካ አንድ ላይ ሆነው የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው ፣ አዲሱ ጠላት የርዕዮተ-ዓለም ሳይሆን በረቀቀ መልክ የሚካሄደው ብዙ አገሮችን ሊያጠቃ የሚችለው የአመጸኞች እንቅስቃሴ እጅግ አደገኛ መሆኑን ያሳስባል። ለዚህም ለስለስ ያሉትን የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችና መሪዎች በሰላሙ እንቅስቃሴ ውስጥ ማካተትና የዓለም ህዝብም በጭንቅላት ውስጥ የገነባውን የጠላትነት ግድግዳ በማፈራረስ አንድ ህዝብ መሆኑን ማየት እንዳለበትና ሰላምን ለማሰፈንና ድህነትን ለማውደም መታገል እንዳለበት አሳሰቧል። እንደዚህ ዐይነቱን የሰላምና የመፈቃቀር ጥሪ ሲያደርግ ከህዝብ ዘንድ የሚሰማው የደስታ ጩኸትና ጭብጨባ ከፍተኛ ነበር። የህዝቡ ጭብጨባ መቀነስ የጀመረው በተለይም ባራክ ኦባማ የጀርመንን ተጨማሪ ዕርዳታና በአፍጋኒስታንም ውስጥ የሚኖራትን ሚና ከፍ ማድረግ አለባት ሲልና ጦርነቱም እዚያ መፋፋም አለበት ብሎ ንግግሩን ሲቀጥል ነው። በተረፈ ግን ያደረገው ንግግር ለብዙዎቹ ተስፋ የሚሰጥና በዚህ ዐይነት ስሜት እንደዚህ ዐይነቱን ንግግር ሊያደርግ የሚችል ፖለቲከኛ በአሁኑ ጊዜ ተፈልጎ መገኘት የማይችል መሆኑን ያረጋገጠበት ነው። በዕወነቱ ይህ ዕለት ለብዙዎቹ ተስፋ የሰጠና በየቡና ቤቱ ሰውን ሲያወያይና በእርግጥም ባራክ ለፕሬዚደንትነት ተመርጦ የአሜሪካንን የውጭ ፖለቲካ ለመለወጥ እንደሚችልና ከእንግዲህ ወዲያም የአሜሪካ የብቸኝነት ጉዞና እዚህና እዚያ ጦርነት መቀስቀሱ እንደሚቆም ህዝቡ ተስፋ እንዳለው መቃኘት ይቻላል። በነጋታው የወጡት የታወቁ ጋዜጦችና የድህረ-ገጽ ዜናዎችም የሚያረጋግጡት የባራክ ኦባማ ንግግር የቱን ያህል የህዝቡን መንፈስ እንዳደሰውና ወደፊትም አሜሪካም መሪነቱን በጋራም ሊወጣ እንደሚችል የሚያረጋግጥ ነው።

የባራክ ኦባማ ወደ አውሮፓና ወደ ማዕከለኛው ምስራቅ መምጣት የሚያመለክተው በውጭው ፖለቲካውም ብቃትነት ያለው መሆኑንና በአሁኑ ወቅት አሜሪካንን እሱና ፓርቲው ብቻ ሊመሩ የሚችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው። የውጭ ፖለቲካንና የአሜሪካንን ሴኪዩሪቲ በሚመለከት በተለይም የሪፓብሊካኑ የፕሬዚደንትነት ተመራጭ አቶ ሜኬን ባራክ ኦባማ ልምድ እንደሌለውና ከኢራንም ሆነ ከኪዩባ መሪዎች ጋር ለማድረግ በሚፈልግው ንግግር የአሜሪካንን ደህንነት ጥቃት ውስጥ እንደሚከታት እያጠነከረ ያወራ ነበር። የወግ አጥባቂዎች አፈቀላጤዎች እንደ ፎክስ ኒውስ የመሳሰሉ የዜና ማሰራጫዎች የባራክን በውጭ ፖለቲካ ልምድ ማጣትና ለእስራኤልም አደጋ ሊፈጥር እንደሚችል የህዝቡን መንፈስ በመረበሽ በሱ ላይ ዕምነታቸውን እንዲያጡ ያልተቆጠበ ቅስቀሳ አድርገዋል። በእርግጥም የአሜሪካንን የዜና ማሰራጫዎች ለተከታተለና በተለይም ሁለቱ የፕሬዚደንት ተመራጮች በአሜሪካን ህዝብ ዘንድ ላይ ያላቸውን ተቀባይነት በየቀኑ እየተከታተሉ ያሚያወጡትን መለኪያዎች ለሚያነብ አቶ ሜኬን በውጭው ፖለቲካው 70% ድጋፍ እንዳለው ፣ በተቀረው የውስጥ ጉዳይ ፖለቲካ ደግሞ ባራክ ኦባማ በከፍተኛ ድምጽ እንደሚቀድም በየጊዜው ይነገራል ። ይህ ዐይነቱ የፖለቲካ ድጋፍ በምርጫው ቀን የቱን ያህል ይመነዘር አይመነዘር እንደሆን ለማረጋገጥ አይቻልም። ይሁንና በዚህ የውጭ ፖለቲካው በአሜሪካን ህዝብ ዘንድ ዕምነት ማጣት ወደ አውሮፓና የማዕከለኛው ምስራቅ መጥቶ መንብኘቱና ከባለስልጣናትም ጋር ንግግር ማድረጉ በውጭ ፖለቲካ ከአቶ ሜኬን

የተሻለ ተቀባይነት እንዳለው አረጋግጧል። በሌላ ኩል ከአሜሪካ ህዝብ ግንዛቤ ማጣት የተነሳና የኮንሰርቫቲቭ የዜና ማሰራጫዎች በሚያደርጉት ቅስቀሳ ይህ የባራክ ኦባማ ጉዞ በዕለት ተዕለት የድምጽ መለኪያው መመዘኛ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳላመጣለት ማንበብ ይቻላል። ሜኬንና የምርጫው አዘጋጅ ኮሜቲም የባራክ ኦባማን የአውሮፓ ጉዞ ልታይ ልታይ ለማለት ያደረገው እንደሆነና እንደ ታወቁት ዘፋኞች ለጊዜው የሰፊውን ህዝብ አመለካከት ሊሰብ የሚችል ነገር ግን ደግሞ አገር ለመምራት ብቃትነት የለውም በማለት ሊያጥላሉት ሞክረዋል።።

ባራክ ኦባማ እንደዚህ ዐይነቱን ተቀባይነት በአውሮፓ ህዝብ ዘንድ ለማግኘት የቻለው ከላይ ከተዘረዘረው መሰረተ-ሃሳብ በመነሳት ብቻ ሳይሆን ብዙው የአውሮፓ ህዝብ የቡሽ-ቼኒ የከረረና የጦረኛ ፖለቲካ ስለሰለቸውም ነው። በተለይም በጀርመን ህዝብ ዕምነት ቡሽና አማካሪዎቹ ከኢራንም ሆነ ከሰሜን ኮሪያ ጋር ሲወዳደሩ ለዓለም ሰላም ጠንቆች ናቸው። ስለዚህም ቡሽና ቼይኒ በመንገዳገድ ላይ ያለውን የአሜሪካንን የበላይነት በጦር ኃይል ተመክተው የአውሮፓን ህዝብ ዝንባሌ ለመሳብና ብቸኛው ኃያል መንግስት እሱ ብቻ እንደሆነ ለማሳመን ያደረጉት ሙከራ ተቀባይነት እንዳላሰገኘላቸው መረዳት ይቻላል። ከቀድሞ የቡሽ-ቼኒ ሰራተኞች እየተጠናቀረ የሚቀርበው ዜናና የሚጽፉትን መጽሀፎችን ለተከታተለ የአሁኑ የአሜሪካን አስተዳደር የቱን ያህል የዓለምን ህዝብ በማታለል የኢራቅን ህዝብ በጦር እንደወረረ ለመረዳት ተችሏል። ስለሆነም የባራክ ኦባማ ብቅ ማለትና የፕሪማሪዩን ምርጫ አልፎ ለፕሬዚደንትነት መወዳደር መብቃቱ የአሜሪካንን የውጭ ፖለቲካ ሊያድስ ይችላል ብለው የሚጠባበቁ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል።

## <u>ባራክ የሚጠበቅበትን ሊያሟላ የሚችል የወደፊቱ ፕሬዚደንት ነው ወይ?</u>

ባራክ ኦባማ የመመረጥ ዕድሉ ከፍተኛ ነው ብለን እንገምት። ከዚህ እርግጠኝነት ተነስተን ህዝቡ በጉጉት የሚጠብቀውንና እሱ ተግባራዊ አደርጋለሁ ብሎ የሚያስበውን ሊያሟላ ይችላል ወይ ? በመጀመሪያ ከሂለሪም ሆነ ከሜኬን ይልቅ ባራክ ኦባማ የአሜሪካን ህብረተሰብ ችግርና ፖለቲካ በርግጥ የገባው አዋቂ ሰው ለመሆኑ ካደረጋቸው መግለጫዎችና ከተካፈለባቸው ክርክሮች መረዳት ይቻላል። ሂለሪም ሆነ ሜኬይን በአሜሪካን የሜይን ስትሪም ፖለቲካ ውስጥ ስላለፉ ወይም በባራክ ኦባማ አነጋገር በዋሽንግተን ፖለቲካ የተቀቀሉ ስለሆኑ ቢመረጡ ተግባራዊ ሊያደርጉት የሚችሉት የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ፖሊሲ ቀድሞውኑ መሰረት ከያዘው የሎቢይስቶች ፖለቲካ በመነሳት እንጂ ጠለቅ ብለው በመሄድ ችግሩን ሊቀርፉት የሚችሉ አይደሉም። በፕሬዚደንት ክሊንተን ጊዜ ታየ የተባለው የኢኮኖሚ ዕድገት ጆርጅ ቡሽ ስልጣኑን ከተረከቡ በኋላ እየተነነ ሊመጣ የቻለው በፕሬዚደንት ሬገን ጊዜ ተግባራዊ እየሆነ የመጣውን ልቅ የገበያ ፖሊሲ በማባባሳቸው ነው። ስለዚህም ነው በፕሬዘደንት ክሊንተን ወቅት ተግባራዊ የሆነው ልቅ የገንዘብ ፖሊሲ የምርት ክንውንን ከማገዙ ይልቅ ወደ ዎል ስትሪት በመሄድ ልዩ የሀብት ሽግሽግ ሊፈጠርና ዛሬ በጉልህ ለሚታየው ጥልቅ የኢኮኖሚ ቀውስ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደረገው። ይህንንም በሚመለከት ባራክ ኦባማ ኒዎርክ በመጋቢት ወር ላይ ተጋብዞ ለድሮ ባለስልጣኖችና ለኒዎርኩ ከንቲባ ለሚስተር ብሉምበርግ ባደረገው ሰፋ ያለና ሳይንሳዊ ንግግር ሁለቱም ፓርቲዎች ለኢኮኖሚው ቀውስ በር የከፈቱ ለመሆናቸውና በተለይም በፕሬዚደንት ሩዘቤልት ጊዜ የወጣውን የባንኮችን የመቆጣጠሪያ ህግ ልቅ በመደረጉና ለዎል ስትሪት ተዋናዮች የሀብት መሸጋሸጊያ መሳሪያ መሆኑን በግልጽ ተናግሯል። በተጨማሪም በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ ፣ በተለይም በዊንፍሪድ ኦፕራ ዝግጅት ላይ ቀርቦ ባደረገው የጥያቄና የመልስ ውይይት የአሜሪካ ኢኮኖሚ ከውጭ በሚመጣ ርካሽ ዕቃ እየተመታ እንደመጣና ብዙ የአሜሪካ ኢንዱስትሪዎችም ወደ ቻይናና ሌሎች አገሮች በመሄድ አሜሪካ ውስጥ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የምርት ክንውን እየተዳከመና ይህም የአሜሪካንን የኢኮኖሚ እያዳከመው እንደመጣ በሰፊው ተንትኗል። ከዚህም በላይ በህብረተሰብ ውስጥ እየጎላ የመጣው የቤተሰብ ቀውስ በዚህ ምክንያት ወጣቱ ወደ አመጽ ማምራትና የህበረተሰቡን የሰላም ኑሮ እያናጋው እንደመጣ በሚገባ እየተገነዘበ ሰው ነው። ችግሩም በተለመደው የቀረጥ መቀነስና መጨመር ዘዴ ሊፈታ እንደማይችል ተረድቷል። ስለሆነም የአሜሪካ ፖሊሲ በተራ በድሮው ዐይነት በፓርቲዎች ፖሊሲና በሎቢስቶች ግፊት ሊለውጥ እንደማይችል በቀጥታም ባይሆን ሂለሪም ሆነ ሜኬን ስር ለሰደደው ኢኮኖሚያውና ማህበራዊ እንዲሁም የባህል ቀውስ መልስ ለመስጠት እንዳማይችሉ ለማሳየት ሞክሯል።

ለባራክ ኦባማ ችግሩን በቀለሉ እንዲቀርፍ እንቅፋት የሚሆነው የቡሽ-ቼኒ አስተዳደር ጥሎለት የሚሄደው የተከሰከሰ ኢኮኖሚ ነው። የውስጡ ኢኮኖሚ ከመዳከሙ የተነሳ የሰፊው ህዝብ የመግዛት ኃይል ተዳክሟል። በፋብሪካዎች ኪሳራ ምክንያት የተነሳ በየጊዜው ከስራው የሚባረረው የሰራተኛ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። የሰፊው ህዝብ የመቆጠብ ኃይል በጣም ተዳክሟል። በብድር በተሰሩ ቤቶች ቀውስ የተነሳ የፊናንስ ገበያው በመፈረካከስ ላይ ይገኛል። የቤቶች ዋጋ ከመውደቁ የተነሳና የሚገዛም ስለሌለ ባንኮች ግራ ተጋብተዋል። ቀውሱን ለማብረድ ከፌዴራል ባንኩ የሚፈሰው ገንዘብ ችግሩን ሊፈታ አልቻለም። ከፍተኛ የዋጋ ግሸበት ፣ በተለይም የቤንዚን ዋጋ መጨመር ህዝቡን አስመርሮታል። የክሬዲት ካርድ ቀውስ በግልጽ እየታየ ነው። የመንግስቱ ባጀት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። በአሁኑ ወቅት ከአራት መቶ ቢሊዮን በላይ የበጀት ዴፊሲት እንዳለ ይታወቃል። የውጭውን ኢኮኖሚ ዘርፍ ለተመለከተ የንግድ ሚዛኑ ክፉኛ ተናግቷል። በሌላ አነጋገር አማሪካ ወደ ውጭ ከምትልከው ወደ ውስጥ የምታስገባው በዐመት ወደ ዘጠኝ መቶ ቢሊዮን ዶላር ይጠጋል። በዚህም ምክንያት ይህንን ቀዳዳ ለመሸፈን ከውጭ ካፒታል መምጣት አለባት። የአገር ውስጥ ሀብት በቻይናና በአረብ አገሮች ገንዘብ እየተገዛ ነው። ወደ ፊት የፖለቲካ ተፅዕኖ ሊያመጡ ይችላሉ የሚል ፍርሃት አለ። በወር ለኢራቅና ለአፍጋኒስታን ጦርነት ወደ አስር ቢለዮን የሚጠጋ ብር ይፈሳል። በዚህ መልክ ነው ባራክ ኦባማም ሆነ ሜኬን የቡሽ-ቼኒ አስተዳደር ጥሎ የሄደውን ቀውስ የሚረከቡት።

ከዚህም በላይ በባራክ የሚመራው መንግስት ይህንን ችግር ለመፍታት ወይም ለማቃለል የቱን ያህል ገፍቶ በመሄድ በሜክሲኮ ፣ በካናዳና በሰሜን አሜሪካ የተመሰረተውንና ለብዙ ሰራተኛ መፈናቀል ምክንያት የሆነውን የነጻ ንግድ ክልል ስምምነት በአዲስ መልክ ሊደራደር ይችላል የሚለው ራሱ የሚያጠያይቅ ሆኗል። ምክንያቱም በአንድ በኩል አሜሪካ እንደዚህ ዐይነቱን ስምምነት በአካባቢም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን እየሰበከች ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ጥያቄ ውስጥ ብታስገባ ሌሎች አገሮችም ወደ ተመሳሳይ እርምጃ ሊያመሩ ይችሉ ይሆናል። ይህ በራሱ ደግሞ የአሜሪካን ትላልቅ ኩባንያዎች የዓለምን ገበያ የመውረር ፍላጎት ሊፃረር ይችላል። ከፖለቲካ አንፃር ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ማለት ነው። ይህንን ትተን ወደ ውስጥ ኢኮኖሚው ስንመጣ ባራክ ኦባማ እንደተለመደው ቀረጥን ለዝቅተኛውና ለማዕከለኛው የህብረተሰብ ክፍል በመቀነስና በሌላ ወገን ደግሞ ከተወሰነ ገቢ በላይ ባላቸው ሀብታሞች ላይ በመጨመር እንደሚለው ኢኮኖሚውን እንዲንሰራራ ለማድረግ ይችላል ወይ? ወይስ ደፍሮ በመሄድ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ የሚያስችለው ሌላ ቆራጥ እርምጃ ይወስዳል የሚለው የሚያነጋግር ሆኗል። አንዳንድ ኢኮኖሚስቶች እንደሚሉት በ1930ዎቹ ዐመታት ፕሬዚደንት ሩዘቤልት ተግባራዊ እንዳደረጉት ዐይነት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ካልተከተለ አሁን ስር የሰደደው ቀውስ ሊፈወስ እንደማይችል ይናገራሉ። ከዚህ ወጣ ስንል ደግሞ የህክምና ዋስትና እንዲደረግለት የሚሻው ወደ 45 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ በአራት ዐመት ውስጥ ህልሙ ዕውን ሊሆን ይችላል ወይ ?

ባራክ ኦባማ ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች በሚገባ የተረዳ ቢሆንም ምኞቱን ተግባራዊ ማድረግ ይችላል ወይ ? ወይስ ሳይወድ በግድ ሎቢየስቶችና ሪፓብሊካኖች በሚያደርጉበት ጫና የተመኘውን ተግባራዊ ሳያደርግ በስም ብቻ በታሪክ ማህደር ውስጥ ስሙ ተጠቅሶ የሚያልፍ ይሆናል ወይ ? በተለይም እንደ አሜሪካና ሌሎችም የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ውስጥ አንድ ፓርቲ ወይም ፕሬዚደንትም ሆነ ወይም ጠቅላይ ሚኒስተር የሚመኘውን ተግባራዊ ሊያደርግ የማይችለው በህብረተሰቡ ውስጥ ተደራጅተው የሚገኙ ኢንስቲቱሽኖችም ሆነ የሲቪሉ ማህበረሰብ ድርጅቶች በርዕዮተ-ዓለም ላይ የተመረኮዘ ፖለቲካ ስለሚያካሂዱና ግፊት ስለሚያደርጉ ነው። በዚህም ምክንያት ፓርቲዎችና ስልጣን የጨበጡ መሪዎች በህገ-መንግስቱ የሰፈነውንና ቃል-ኪዳን የገቡለትንና የሁሉንም ህብረተሰብ ክፍል ጥቅም እንጠብቃለን ያሉትን እየጣሱ እንዲመጡ ይገደዳሉ። በተለይም የኒዎ-ሊበራል ርዕዮተ-ዓለም በኢንስቲቱሽን ደረጃ ስር በሰደደበት ቦታና እንዲሁም በከበርቴዎች በሚደጎሙበት አገር ሌላ ሰፊውን ህዝብ ሊጠቅምና ኢኮኖሚውን እንዲንሰራራ ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ ለማውጣት ችግር ውስጥ የተገባበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በዚህ ላይ በየጊዜው እየረቀቁ የሚወጡት የተወሳሰቡ ፖሊሲዎችና ህጎች የጠቅላላውን ህብረተሰብ ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ በአማዛኙ ሀብት ከዝቅተኛው የህብረተሰብ ክፍል ወደ ላይ በተለያዩ መሳሪያዎች እንዲሸጋሸጉ የሚያደርጉ ናቸው። በዚህ ምክንያት መንግስትና ፓርቲዎች የሎቢስቶች መጨፈሪያ በመሆን ሰፊው ህዝብ ለፖለቲካ ያለውን ፍላጎት እያዳከሙና የፈለጉትን ይስሩ እያሉ ተስፋ እያስቆረጡዋቸው ከዐመት ወደ ዐመት የህዝቡ

የመምረጥ ኃይል እየቀነሰ በመምጣት ላይ ነው ። ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ከከበርቴው ፓርቲዎች ይልቅ ቀኞችና በጣም አክራሪ ፓርቲዎች ተደማጭነት እያገኙ ሊመጡ ችለዋል። አሜሪካ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ የሁለት ፓርቲ ስርዓት ቢታይም አደጋው ሁል ጊዜ ሊከሰት የሚችለው ከዚያው ከስርዓቱ ውስጥ ነው። በዚህም ምክንያት እንደ ባራክ የመሳሰሉት ቀናና ብልህ አስተሳሰብ ያላቸው የሚፈልጉትን በቀላሉ ተግባራዊ ሊያደርጉ የማይችሉበት ሁኔታ አለ ማለት ነው። ይህንንም በመረዳት ነው በፕሪማሪይው የምርጫ ሂደት ውስጥ የሻገተውን ፖለቲካ ለመስበር ይበልጥ በወጣቱ ላይ ዕምነቱን የጣለውና ማንቀሳቀስ የጀመረው።

ሰሞኑን ያለውም ውዝግብም ባራክ አባማ ይበልጥ በወጣቱ ላይና እሱ ባደራጀው ምስጢራዊ ነው ብለው በሚያስቡት እንቅስቃሴና የሱ የምርጫ ኮሚቴ ዋና አደራጅ ላይ በመመካቱ ኢስታብሊሽሜንቱን ቦታ አይሰጠውም የሚል ፍርሀት አለ። ሰለሆነም ባራክ ዋሽንግተን ተረጋግተው የተቀመጡትን ፖለቲከኞች እየረሳ በመምጣት ላይ ነው እያሉ በማስወራት ስትራቴጂውን እንዲለውጥ እያሰገደዱት ነው። ከክሊንተንም ሆነ ከድሮ ስታብሊሽመንቶች አንዳንድ ሰዎችን እያካተተ ነው። ይህ ዐይነቱ የተጠንቀቀ ፖለቲካ ከአደጋ ሊያድነው ይችላል።

ወደ ኢኮኖሚው ስንመጣ አሜሪካን በቴክኖሎጂም ሆነ በሰው ዕውቀት ከፍተኛ ፖቴንሺያል አላት። ግሩም ግሩም ሃሳቦችም ይሰነዘራሉ። የህብረተሰባቸውንም ችግር በደንብ የገባቸው ከነጩም ሆነ ከጥቁሩ የህብረተሰብ ክፍል ብቅ ያሉና በዕውቀታቸው ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው ብዙ ምሁራን እንዳሉ የሚታተሙትን መጽሀፎችና የሚደረጉትን ውይይቶችና ክርክሮች ለተመለከተ ሊገነዘብ ይችላል። ይሁንና የቀኞች ርዕዮተ-ዓለም በመጠናከሩ ከታች የሚቀርቡት ሃሳቦችና የሚሰጡ አስተያየቶች እስካሁን ድረስ ቦታ አልተሰጣቸውም። በዚህም ምክንያት ስር የሰደደውን የኒዎ-ሊበራል ርዕየተ-ዓለም ለመስበርና መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ያስቸግራል። እንደ ማንኛውም ህብረተሰብ በአሜሪካ ውስጥ ያለው ችግር ፣1ኛ) በተማረው የህብረተሰብ ክፍልና በሰፊው የህብረተሰብ ክፍል ያለው ሰፋ ያለ የእውቀት ልዩነት አለ ፤ 2ኛ) ቀስ በቀስ የፖለቲካ ስልጣኑን የሚይዙና ከሎቢስቶች ጋር የተቆራኙ ፓርቲዎች ከህብረተሰቡ ፍላጎት እየተነጠሉ በመምጣታቸው ግሩም ግሩም ፖሊሲዎች ቢኖሩም እነሱን ተግባራዊ ለማድረግ በፍጹም አይቻልም። ስለዚህም ይህ ዐይነቱ የፖለቲካ አወቃቀርና በተለይም ደግሞ ህዝቡን አደንቁሮ ለማስቀረት በሪፓብሊካን ፓርቲው የሚደረገው አጉል የአገር ወዳድነት ዘመቻ ካልደከመ የህብረተሰቡ ችግር ለጊዜው ገብ ቢልም እንደገና እየተመላለሰ በመምጣት ሲፈታተነው ይኖራል። ከዚህ ችግር ለመውጣት ነው እንግዲህ ባራክ አባማ ከተመረጠ የሚያስቸግረው። ስለሆነም አሁንም ቢሆን በተለይም የጦር መሳሪያ ሎቢስቶችና የፊናንስ ኦሊጋርኪዎች ታክቲክ ፖሊሲውን ወደ ውጭ እንዲያተኩርና ውስጥ ያለው ቅራኔ እንዲባባስ ሳይወዱ በግድ ይገፋፉታል። ይህ ደግሞ በታሪክ የተረጋገጠ ነው። የፈለገውን ያህል ዲሞክራሲያዊ ኢንስቲቱሽን አለ ቢባልም ከረጅም ጊዜ አንስቶ ውስጥ ለውስጥ ሲደራጁ የከረሙና በብዙ ሺህ ሰንሰለት የተሳሰሩ ባገኙት ጥቅምና የኑሮ ደረጃ እየታወሩ ነገሩ እንዲባባስ ከማድረግ አይቆጠቡም። በቶኒ ብሌር የሚመራው የአዲሱ ሌበር ፓርቲ በአስር ዐመት ውስጥ የሰራውን ወንጀልና አሁን ፓርቲው ያለበትን ሁኔታ መመልከት ይበቃል። ቶኔ ብሌር የተከተለው ፖሊሲ የወይዘሮ ቴቸርን የቀኝ የገበያ ፖሊሲ በማጠንከርና ሀብት ከደሀው ወደ ሀብታሙ እንዲሸጋሸግ በማድረግ ነው። ይህ ዐይነቱ ፖሊሲ ያስከተለው ውጤት በለንደን ከተማ በተለይም የወጣት ወንጀለኞችን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አድርጓል። የኑሮ ውድነት ከምን ግዜውም በላይ ጨምሯል። እንደዚህ ዐይነቱ ወደ ቀኝ ጭልጥ ብሎ የመሄድ ፖሊሲ በባራክ አባማ ዘመን ሊከሰት ባይችልም ህልሙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚገጥመው ችግር ቀላል አይሆንም ማለት ነው።

## <u>የመመረጥ ዕድሉ የቱን ያህል ነው?</u>

እሳካሁን ድረስ ባራክ ያለበት ችግር በተለይም ባልተማረው ወይም ብሉ ከለር በተባለው ሰፊው የህብረተሰብ ክፍል ተደማጭነት ለማግኘት ያለመቻል ነው። ኮንሰርቫቲቮች አሁንም ቢሆን ቀደም ብለው እንዲሚሸርቡት ተንኮል በማስፈራራት የባራክን የመመረጥ ዕድል ሊዘጉበት ይችላሉ። የዛሬ አራት ዐመት ሚስተር ኬሪ ከቬትናም ጋር በተያያዘ ጦርነትና አገር ወዳድ አይደሉም በሚል ምርጫውን ሊሸነፉት የበቁትና የአሜሪካንም ፖለቲካ እንደገና በቡሽ-ቼኒ እጅ ወድቆ ህብረተሰቡ መቀመቅ ውስጥ ሊገባ የቻለው የአሜሪካን ህዝብ ዕውነትን ከዕውሸት ለመለየት ያለው ኃይል ደካማ በመሆኑ ነው። በቀን ስንትና ስንት ኪሎ ሜትር እየተጓዘ አስራ ሁለት ሰዓት የሚሰራ ሰራተኛ ይህ ዐይነቱ

የፖለቲካ ትብትብ ሊገባው አይችልም። እዚህ ላይ ከሰላሳ በላይ የቴሌቪዥን መስመርና ዝባዝንኪ ፕሮግራሞች እየተቀያየሩ በሚታዩበት አገር የሰው የማሰብ ኃይል በመዳከም ዕውነቱን ከውሸት የመለየት አቅም አይኖረውም። በዚህም ምክንያት ባራክ ኦባማ ይህንን ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል ለመሳብና ለማሳመን ትልቅ ስራ መስራት ይኖርበታል። ኢሊት እንዳልሆነና ከጎናቸው የቆመ መሆኑን ማሳመን አለበት። ሌላው የባራክ ችግር በተለይም የነጩን ፖለቲካ ከሚጠሉ አክራሪ ከሚመስሉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የሚሰነዘረው ኃይለ-ቃል ነው። ጊዜያችን ደርሷል፤ ኋይት ሃውስን መንጠቅ አለብን የሚለው ቦታ የሌለው አነጋገርና ሙዚቃ ነጩን ሊያስፈራው ይችላል። ሊበራል የሚባለውና እሱን ሊመርጥ የተዘጋጀው ወደ መጨረሻው ላይ ሊከዳው ይችላል። እነዚህን መቋቋም ከቻለና የሰፊውን ህዝብ መንፈስ ረጋ የሚያስደርግ ፖለቲካ ከተከተለ የመመረጥ ዕድሉ ከፍተኛ ነው። አንዳንድ የአውሮፓ ታዛቢዎች እንደሚሉት የአሜሪካን ህዝብ ይህንን ታሪካዊ ዕድል ተጠቅሞ ባራክን ካልመረጠ ሊወጣው የማይችለው ትልቅ ቀውስ እንሚገባ ያትታሉ።

በተለይም አሜሪካን የሚኖሩ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ባለፈው ሰባት ወር ለባራክ ኦባማ ብዙ ስራዎች እንደሰሩ ይታወቃል። ባራክ ቢመረጥ ምናልባት አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ የሚኖራት ፖለቲካም ሊለወጥ ይችላል ብለው በመገመት ነው። በእርግጥ ባራክ ቢመረጥ በምንም ዐይነት የከረረ የውጭ ፖለቲካ አያካሄድም። በሌላ ወገን ግን ባለበት ግፊትና የኃይል አሰላለፍ የውጭው ፖሊሲው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ይህንም ያህልም ግፊት ሊኖረውና እነ መለስን ርህሩህ ሊያደርጋቸው አይችልም። ይህ ዐይነቱ የፖለቲካ ስሌት ቢገባኝም በክሊንተን ጊዜ እንዳየነው ከባራክም ብዙም የምንጠብቀው ነገር በፍጹም አይኖርም። ስለዚህም የኛ ፖለቲካ ትግል በራሳችን ዕውቀትና ኃይል ብቻ ላይ መተማመን ነው ያለብን። ይህ ማለት ግን ከውጭ ረገብ ያሉ የፖለቲካ ሂደቶችን ተጠቅመን ቅስቀሳ አናድርግ ለማለት አይደለም። ለማለት የምፈልገው ከትውልድ ትውልድ የተዘናጋ የየዋሆች ፖለቲካ ማካሄድ የለብንም። ማንኛውም አገር ብሄራዊ ነፃነቱን ሊያሰከብርና ወደ ውስጥ ደግሞ ዲሞክራሲያዊና ነፃ ስርዓት ሊገነባ የሚችለው በራሱ የተማመነ እንደሆነ ብቻ ነው። ያም ሆነ ይህ ባራክ ኦባማ የሚቀጥለው የአሜሪካ ፕሬዚደንት እንዲሆን እንጸልይለት። ከጎኑም እንቁም !!

**ፈቃዱ በቀለ**